# የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ

# የግል ጽዳት ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት አሰጣጥ አሠራር መመሪያ

## (መመሪያ ቁጥር 157/2016)

ሚያዚያ 2016 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## መግቢያ፡-

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የከተማ አስተዳደሩ ተቋማትን መልሶ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 እንደተሻሻለ አንቀጽ 53 መሰረት ደረቅ ቆሻሻን ለማስተዳደር ስልጣን የተሰጠው ተቋም ነው ፡፡ በተሰጠው ስልጣን መሰረተ የተቀናጀ ደረቅ ቆሻሻ አስተዳደርን ለማስፈን እና የተሰጠውን ተልዕኮ ለማሳካት እና ራዕዩን እውን ለማድረግ የሚያስችሉ የህብረተሰቡን ግንዛቤ የማሳደግ፣ ፈጣን የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት የበመስጠት፣ ደረቅ ቆሻሻን ጥቅም ላይ የማዋልና መወገድ የሚገባውን ደረቅ ቆሻሻ ጤናማ በሆነ መልኩ የማስወገድ አሰራሮችን በመተግበር ላይ ይገኛል ፡፡ ከሚሰጣቸው በርካታ የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎቶች መካከል  በቀጥታ ከህብረተሰቡ ጋር ግንኙነት ያላቸውና የቅሬታ ምንጭ የሆኑት ደረቅ ቆሻሻን የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎቶች ናቸው ፡፡ ከ650 ሽ በላይ ለሚሆኑ አባዋራዎች/እማዋራዎች እና ከ9 ሽ በላይ ለሚሆኑ ተቋማት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ለማጓጓዝ በመንግስት አቅም ብቻ ሊሰራ የማይችል በመሆኑ ኤጀንሲው በሚከፍለው የአገልግሎት ክፍያ ተመን መሰረት አገልግሎቶቹ በሶስተኛ ወገን እንዲሰጡ ተደርጓል ፡፡ ከመኖሪያ ቤቶች የሚመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በጥቃቅንና አነስተኛ የተደደራጁ ዜጎች ቤት ለቤት እየሄዱ የመሰብሰብ አገልግሎቱን እንዲሰጡ ሲደረግ ከመኖሪያ ቤት ውጪ ላሉ ተቋማትና ድርጅቶች ደግሞ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ እንዲሰማሩ በተፈጠረው ምቹ ሁኔታ መሰረት በርካታ የግል የጽዳት ድርጅቶች በህጋዊ መንገድ ተመዝግበው ደረቅ ቆሻሻን ከተለያዩ ተቋማት በመሰብሰብና በማጓጓዝ አገልግሎት እየሰጡ ይገኛሉ፡፡
ነገር ግን ለጥቃቅንና አነስተኛ ጽዳት ሽርክና ማህበራት የአሰራር መመሪያ የተዘጋጀ ቢሆንም የግል የጽዳት ድርጅቶች ለማስተዳደር የአገልግሎት አሰጣጥ መመሪያ ባለመኖሩ በግል ጽዳት ድርጅቶች የሚሰጠው አገልግሎት እንዴት እንደሚሰጥና በአገልግሎት አሰጣጡ የሚፈጠሩ የአሰራር ግድፈቶች እንደት ይታረማሉ የሚለውንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች ለመተግበር አስቸጋሪ ሆኗል ፡፡ ስለዚህ ይህንን ችግር በዘላቂነት ለመፍታትና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጥ አገልግሎት ለመስጠት እንዲያስችል የየግል የጽዳት ድርጅቶች የአገልግሎት አሰጣጥ የአሰራር መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል ፡፡

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አሰፈፃሚ አካላትን መልሶ ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 74/2014 እንደተሻሻለ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 2 (ሠ) በከተማው ካቢኔ በተሰጠው መመሪያ የማውጣት ስልጣን መሰረት ይህን የግል የጽዳት ድርጅቶች የአሰራር መመሪያ አውጥቷል፡፡

# ክፍል አንድ
# ጠቅላላ ድንጋጌዎች

## 1. አጭር ርዕስ

- ❖ ይህ መመሪያ የግል ጽዳት ድርጅቶች የአገልግሎት አሰጣጥ አሰራር መመሪያ ቁጥር 157/2016'' ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡

## 2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1. ***"ኤጀንሲ"*** ማለት የአዲስ አበባ ከተማ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ነው፤
2. **"ደረቅ ቆሻሻ"** ማለት ከመኖሪያ ቤት፣ ከንግድ ማዕከላት፣ ከኢንዱስትሪ እና ከተለያዩ ተቋማት በሰው እና በእንስሳት እንቅስቃሴ የሚፈጠር ጥቅም የማይሰጥ ወይም የማይፈለግ ተብሎ የሚጣል ጠጣርና ከፊል ጠጣር የሆነ ቁስ ነው፡፡
3. **"መሰብሰብና ማጓጓዝ"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን ከምንጩ ከተቋማት (ከሆቴል፤ ከንግድ ማዕከላት፤ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ወዘተ) ሰብስቦ ወደ መጨረሻ መዳረሻ ማቃጠያ ማዕከል፤ ወይም መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት ወይም ማስወገጃ ቦታ በራስ ተሽከርካሪ ማጓጓዝ ነው፡፡
4. **"የግል የጽዳት ድርጅት"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን በአዲስ አበባ ከተማ ከሚገኙ የተለያዩ ተቋማት የመሰበስብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጡ በግል፤ በማህበር፤ በሽርክና፤ በዩኒዬን፤ ወዘተ የተደራጀ ድርጅት ነው፡፡
5. **"ተሽከርካሪ"** ማለት ደረቅ ቆሻሻን ወደ ማስወገጃ ቦታ ወይም ማቃጠያ ማዕከል የሚጓጓዝበት የግል የጽዳት ድርጅት ኮምፓክተር ተሽከርካሪ ነው፡፡
6. **"የስራ ፈቃድ"** ማለት የጽዳት አስተዳዳር ኤጀንሲ ለግል የጽዳት ድርጅቶች የሚሰጠው በከተማው ውስጥ ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ የስራ ፈቃድ ነው ፡፡
7. **"ተቋም"** ማለት በከተማችን ውስጥ ከመኖሪያ ቤት ውጭ የሆኑ መንግስታዊና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፤ የንግድ ማዕከላት፤ ሆቴሎች፤ ሆስፒታሎች፤ አነስተኛና ከፍተኛ የንግድ ቤቶች፤ ትምህርት ቤቶች፤ የመንግስት መስሪያቤቶች፤ ወዘተ ያጠቃልላል፡፡

## 3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ከተቋማት ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብና ማጓጓዝ አገልግሎት ላይ በሚሰሩ በሁሉም የግል የጽዳት ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

# ክፍል ሁለት

## <u>ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ</u>

## 4. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት አሰጣጥ

ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት፡-

1. ከመኖሪያ ቤት ወጪ ለሆኑ በየደረጃው ተለይተው የተሰጡትን መንግስታዊና መንግስታዊ ላልሆኑ ተቋማት በሙሉ ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት ይሰጣል ፡፡ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎቱ የሚሰጠው ቤት ለቤት (ተቋም ለተቋም) በመሄድ ይሆናል ፡፡
2. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና ማጓጓዝ አገልግሎቱን በቆሻሻው አይነትና መጠን መሰረት ይሰጣል፤

ሀ) በቀላሉ በጥቃቅን ተዋህሲያን (ባክቴሪያ) አማካይነት የሚበሰብሱ ቆሻሻዎችን (የምግብ ተረፈ ምርት፣ የአትክልት ተረፈ ምርት፣ ዝቃጭነት ያላቸውን ቆሻሻዎች) በየቀኑ የሚሰበሰብና የሚያጓጉዝ ይሆናል፤

ለ) ተቋሙ የሚያመነጨው ደረቅ ቆሻሻ ማንኛውም የቆሻሻ አይነት ሆኖ መጠኑ ግን 8 ቶን ወይም 40 ሜ.ኩ. የሚሆን ከሆነ የግል ጽዳት ድርጅቱ ለተቋሙ በየቀኑ አገልግሎቱን ይሰጣል፤

ሐ) ለሎች ደረቅ ቆሻሻዎችን እንደሁኔታው በሳምንት አራት ጊዜ፣ ሶስት ጊዜ፣ ወዘተ ይሰጣል ፡፡ ነገር ግን ቢያንስ በሳምንት ሁለት ጊዜ አገልግሎቱን ይሰጣል፤ ፡

መ) አገልግሎቱን ከሚሰጠው ተቋም ጋር አገልግሎቱን እንዴትና መቼ እንደሚሰጥ በሚያደርገው ስምምነት መሰረት አገልግሎቱን በስታንዳርድ ይሰጣል፤

3. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተቋማት ኤጀንሲው ይመድብለታል ፡፡
4. ኤጀንሲው የመደበለትን ተቋማት ተቋማቱ የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ መጠን፣ አይነት፣ ወዘተ (ማለትም ቆሻሻው ክብደት አለው፣ ቆሻሻው ቀላል ነው፣ ወዘተ.) መሰረት ሳያደርግ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅበታል፤
5. ኤጀንሲው የመደበለትን ተቋማት በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ስለመመስጠቱ በዚህ መመሪያ በቅጥያ ሁለት (annex two) በተያያዘው ቅጽ መሰረት በየወሩ ከተቋማቱ ማረጋገጫ ያቀርባል፡ መረጃውንም በሶስት ኮፒ ሰርቶ አንዱን ለወረዳ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት፤አንዱን ለኤጀንሲው፤ አንዱን ለራሱ ያስቀራል፡
6. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጠው በኮምፓክተር ተሽከርካሪ ይሆናል ፡፡ ነገር ግን ወደ ውኃነት ያደላ ደረቅ ቆሻሻ/ የፋብሪካዎች ዝቃጭ (የፋብሪካ ቆሻሻ፣ የመጠጥ ፋብሪካ፣ የቄራ ተረፈ ምርት፣ ወዘተ/ የሚሰበስብና የሚያጓጉዝ ከሆነ በገንዳ ማንሻ ተሽከርካሪ ያጓጉዛል፤ ገንዳውም ሙሉ በሙሉ በሸራ መሸፈንና ለእይታና ለአካባቢ ተስማሚ መሆን አለበት ፡፡
7. ደረቅ ቆሻሻ በሚያጓጉዝበት ተሽከርካሪ ላይ በግራና በቀኝ ጎኑ በጉልህ ጽሑፍ (በሩቅ በሚነበብ መልኩ) የድርጅቱን ስም መለጠፍ አለበት፤
8. ደረቅ ቆሻሻ በማጓጓዝ ያሰማራቸው ተሽከርካሪዎች ጽዳታቸው የተጠበቀ መሆን አለበት፤
9. የተሽከርካሪ ብልሽት ከገጠመው በኪራይ ወይም በተውስት አገልግሎቱን ሳይቆራረጥ መሸፈን አለበት፤ ነገር ግን አገልግሎት መስጠት የማያስችለው ሁኔታ ሲፈጠር ወዲያውኑ ለኤጀንሲው አሳውቆ ተቋማቱ አገልግሎት እንዲሰጣቸው ማድረግ አለበት ፡፡
10. ለኤጀንሲው አሳውቆ በተለያዩ ምክንያቶች አገልግሎት መስጠት አቋርጦ ወደ ስራ እንደገና መግባት ከፈለገ ኤጀንሲው የሚጠብቀው እስከ ሁለት ወር ብቻ ነው ፡፡
11. ለኤጀንሲው ሳያሳውቅ አገልግሎት ሳይሰጥ አንድ ወር ካለፈው ወዲያውኑ የስራ ውሉ እንዲቋረጥ ይደረጋል ፡፡

12. ከኤጀንሲው ጋር የነበረው የስራ ውል ከተቋረጠ እንደገና ወደ ስራ መግባት የሚችለው እንደ አዲስ የግል ጽዳት ድርጅት ተመዝግቦና የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ሲሰጠው ይሆናል ፡፡

13. ኤጀንሲው የማጓጓዝ ስራው ችግር ሲገጥመው የግል ጽዳት ድርጅቱ ቀደም ሲል ከተመደበበት ክፍለ ከተማ ውጪ ለአጭር ጊዜ (ለ15 ቀናት) ሌላ ክፍለ ከተማ ሲመድበው በተመደበበት ክፍለ ከተማ የማጓጓዝ አገልግሎትቱን የመስጠት ግዴታ አለበት፤

## 5. <u>የስራ ውልና እድሳት</u>

ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት፡-

1. የአገልግሎት ክፍያ የሚፈጽምለት ኤጀንሲው ስለሆነ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተቋማት ኤጀንሲው ከተመደቡለት በኋላ ከኤጀንሲው ጋር ህጋዊ የስራ ውል ስምምነት ይፈራረማል፤
2. የስራ ውል ስምምነት ከኤጀንሲው ጋር በየዓመቱ ያድሳል፤
3. የስራ ውል ፈቃድ እድሳት በሚቀጥለው በጀት ዓመት ከሀምሌ 1-30 ባሉት ቀናት ያከናውናል፡፡ ይህም ማለት የሀምሌ ወር ክፍያ ከመከናወኑ በፊት ሁለቱም ተዋዋዬች ውላቸውን ማደስና መፈራረም አለባቸው ፡
4. ውል ሳያድስ የአገልግሎት ክፍያ መጠየቅ አይችልም፤ ክፍያም አይፈጸምም፡፡
5. የስራ ውል ፈቃዱ ከኤጀንሲው ጋር ለማደስ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን መስፈርቶች ማሟላት ይገባዋል፡፡

   ሀ/ ከኤጀንሲው የተሰጠው የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ሰርትፍኬት

   ለ/ አገልግሎት እንዲሰጥ ከተመደበበት ክፍለ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ስራውን እንዲቀጥል የሚያስችል የድጋፍ ደብዳቤ፤

   ሐ/ ከመጨረሻ ደረቅ ቆሻሻ መዳረሻ ማዕከላት (ላንድፊል፣ ኃይል ማመንጫ፣ ኡደት ማዕከላት) የመልካም ስራ አፈጻጸም የድጋፍ ደብዳቤ፣

   መ/ የታደሰ የንግድ ፈቃድ፣

   ሠ/ ዓመታዊ የተሸከርካሪ ቴክኒካል ምርመራ ውጤት፣

   ረ/ የሶስተኛ ወገን ኢንሹራንስ፣

ሰ/ በአገልግሎት አሰጣጡ ጉደለት ተገኝቶበት በኤጀንሲው ምንም አይነት ቅጣት/እርምጃ ያልተወሰደበት መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ፤

## 6. የአገልግሎት ክፍያ

1. ወሩ ካለቀ በኋላ በሚቀጥለው ወር ከ1 - 5 ባሉት ቀናት እያንዳንዱ የግል ጽዳት ድርጅት አስፈላጊ መረጃዎችን አሟልቶ የአገልግሎት ክፍያ እንዲከፈለው በደብዳቤ ይጠይቃል ፡፡ መሟላት ያለባቸው መረጃዎች፡

ሀ/ በኤጀንሲው የተመደቡለትን ተቋማት በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ስለመስጠቱ ከክፍለ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ማረጋገጫ ደብዳቤ፤

ለ/ አገልግሎት ከሚሰጣቸው ተቋማት ተገልጋዮችን በሚያረካ መልኩ አገልግሎት ስለመስጠቱ በዚህ መመሪያ በቅጥያ ሁለት (annex two) በተያያዘው ቅጽ መሰረት የማረጋገጫ ሰነድ፤

ሐ/ በወሩ ሰብስቦ ያጓጓዘውን ደረቅ ቆሻሻ መጠን የሚያሳይ ሰነድ፤

2. በየቀኑ በግል ጽዳት ድርጅት ተሰብስቦ የተጓጓዘውን ደረቅ ቆሻሻ ከላንድፊል በሚላከው ደረሰኝ (መረጃ) መሰረት በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት የሚገኘው ዳታቤዝ ባለሙያ መረጃውን ያደራጃል፤ ወደ መረጃ ቋት ያስገባል፤
3. የኤጀንሲው ዳታቤዝ ባለሙያ በግል ጽዳት ድርጅት የቀረበውን የክፍያ ጥያቄ ትክክለኛነት ከላንድፊል በመጣው መረጃ መሰረት ያረጋግጣል፡
4. የግል የጽዳት ድርጅት ደረቅ ቆሻሻ ሰብስቦ ላጓጓዘበት የክፍያ ተመን የከተማው አስተዳደር በሚወስነው ቁርጥ ዋጋ መሰረት በሜትር ኩብ ወይም በኪሎ ግራም ተሰልቶ ይሆናል;
5. የግል የጽዳት ድርጅቶች ሰብስበው ለሚያጓጉዙበት ክፍያ ተመን ዋጋ በጥናት የተመሰረተና ከወቅቱ ሁኔታ ጋር ያገናዘበ የዋጋ ተመን የከተማው አስተዳደር ሊጨምር ወይም ሊቀንስ ይችላል;

6. የደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት ክፍያ ዋጋ ማሻሻያ ማድረግ ሲያስፈልግ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የአገልግሎት ክፍያ ዋጋ ተመን የሚያጠና ኮሚቴ አቋቁሞ በኮሚቴ እንዲጠናና የጥናቱ ውጤትም በከተማው ፋይናንስ ቢሮ እንዲጸድቅ ያደርጋል ፡፡
7. በግል ጽዳት ድርጅቶች ለሚሰበሰብና ለሚጓጓዝ የደረቅ ቆሻሻ የክፍያ መጠኑ ክፍለ ከተሞች ከላንድፊል ባላቸው እርቀት መሰረት እሩቅ ክፍለ ከተማ እና ቅርብ ክፍለ ከተማ ምድብ ተብሎ ይለያያል ፡፡ አሁን ካለው የደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ እሩቅ ምድብ ክፍለ ከተሞች ለሚኩራ፣ የካ፣ ቦሌ፣ አቃቂ ቃሊቲ እና ጉለሌ ሲሆኑ ቅርብ ምድብ ክፍለ ከተሞች ደግሞ አራዳ፣ አዲስ ከተማ፣ ኮልፌ ቀራኒዮ፣ ልደታ፣ ቂርቆስና ንፋስ ስልክ ላፍቶ ናቸው ፡፡
8. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት የማስወገጃ ቦታ አግልግሎት ክፍያ ኤጀንሲው በሚያወጣው ታሪፍ መሰረት የመክፈል ግዴታ አለበት ፡፡

## ክፍል ሶስት፡

## በደረቅ ቆሻሻ አስተዳደር ዘርፍ የተሰማሩ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

7. <u>የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት</u>
    1. የተለያዩ የለአሰራር መመሪያዎችንና ስታንዳርዶችን ያዘጋጃል፣
    2. በግል ጽዳት ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተቋማት መረጃ ያደራጃል፤
    3. ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተቋማት በተለያዩ መስፈርቶች ለግል ጽዳት ድርጅቶች ይመድባል፤
    4. ለግል ጽዳት ድርጅቶቹ የብቃት ማረጋገጫና የስራ ፈቃድ ይሰጣል፤
    5. ከግል ጽዳት ድርጅቶች ጋር ህጋዊ የስራ ውል ይዋዋላል፤ በየአመቱም የውል እድሳት ያደርጋል፤
    6. ለግል ጽዳት ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻ ለሰበሰቡበትና ላጓጓዙበት በየወሩ ከተመደቡበትና ከሚሰሩበት ክ/ከተማ የተረጋገጠ ሰነድ ሲያቀርቡና ትክክለኛነቱ በኤጀንሲው በደረቅ ቆሻሻ አገልግሎት አሰጣጥ ዳይሬክቶሬት ዳታቤዝ ባለሙያ ሲረጋገጥ በውሉ መሰረት የአገልግሎት ክፍያ ይከፍላል፤
    7. የግል ጽዳት ድርጅቶች በሚሰጡት አገልግሎት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፤

8. ለክፍለ ከተሞችና ለወረዳዎች ክትትልና ድጋፍ ያደርጋል፤ ስለግል ጽዳት ድርጅቶች አግለግሎት አሰጣጥ በዚህ መመሪያ በቅጥያ ሶስት (annex three) በተያያዘው ቅጽ መሰረት በየወሩ ከክፍለ ከተሞች ሪፖርቶችን ይቀበላል፡፡
9. በገቡት ውልና በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት በማይሰጡ የግል ጽዳት ድርጅቶች ላይ ውል እስከ መሰረዝና ከስራ እስከ ማስወጣት ድረስ የተለያዩ እርምጃዎችን ይወስዳል፤
10. ለግል ጽዳት ድርጅቶች የግንዛቤ ማስጨበጫ ስልጠናዎችን ይሰጣል፤
11. ኤጀንሲው በማዕከል ደረጃ የያዛቸውን ኃላፊነትና ተግባር እንደስፈላጊነቱ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ወደ ታችኛው መዋቅር ሊያወርድ ይችላል፡፡

8. **<u>የክፍለ ከተማ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. በክፍለ ከተማው በግል ጽዳት ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተቋማት በዚህ መመሪያ ቅጥያ ሶስት (annex three) ተሞልቶ ከወረዳ በሚመጣለት መረጃ መሰረት መረጃ ያደራጃል፤ ለኤጀንሲው ሪፖርት ያደርጋል፤
2. በክፍለ ከተማው ተመድበው የሚሰሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት በስታንዳርዱ መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ፤ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ የአፈጻጸማቸውን ሪፖርት አጠናክሮ በዚህ መመሪያ በቅጥያ ሶስት (annex three) በተያያዘው ቅጽ መሰረት በየወሩ ለኤጀንሲ ይልካል፡፡
3. ከተገልጋዩ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ለይቶ ወቅታዊ ምላሽ ይሰጣል፡፡ በክፍለ ከተማው ከሚገኙ ከግል የጽዳት ድርጅቶች ጋር በቋሚነት ስራዎችን ይገመግማል አስፈላጊውን ማስተካከያም በመሪያው መሰረት ያደርጋል፡
4. በየወሩ የግል የጽዳት ድርጅቱ በተመደበበት ተቋም በአግባቡ ለማገልገሉ አረጋግጦ የክፍያ ሰነዱ ተገቢ መሆኑን ለኤጀንሲው በሸኝ ደብዳቤ ወር በገባ እስከ አምስት ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ይልካል፤

9. <u>የወረዳ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. በወረዳው በግል ጽዳት ድርጅቶች ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት የሚሰጣቸውን ተቋማት መረጃ በቅጥያ ሶስት (annex three) መሰረት አደራጅቶ ለክፍለ ከተማው ሪፖርት ያደርጋል፤
2. በወረዳው ተመድበው የሚሰሩ የግል የጽዳት ድርጅቶች የሚሰጡት አገልግሎት በስታንዳርዱ መሰረት እየተሰራ ስለመሆኑ ተከታታይነት ያለው ድጋፍ፤ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡ የአፈጻጸማቸውን ሪፖርት አጠናክሮ በዚህ መመሪያ በቅጥያ ሶስት (annex three) በተያያዘው ቅጽ መሰረት በየወሩ ለክፍለ ከተማው ሪፖርት ያደርጋል፡፡
3. በወረዳው የሚገኙ የህብረት ሽርክና የጽዳት ማህበራት ከመኖሪያ ቤት ውጭ (ከተለያዩ ተቋማት፤ የንግድ ድርጅቶች) ደረቅ ቆሻሻ እንዳያነሱ/እንዳይሰበስቡ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊውን ማስተካከያ ይወስዳል፤

10. <u>የግል ጽዳት ድርጅቶች ተግባርና ኃላፊነት</u>

ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት፡-

1. ወደ ማስወገጃ ቦታ፤ ማቃጠያ ማዕከላት ወይም ለመልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከላት የሚጓጓዙ ደረቅ ቆሻሻዎች ኤጀንሲ ባወጣው ደንብ፤ መመሪያ፤ ስታንዳርድና ማኑዋል መሰረት ማከናወን ይገባዋል፡፡
2. በየዓመቱ ከኤጀንሲው ጋር በዚህ መመሪያ መሰረት የስራ ውሉን ማደስና የመፈራረም ግዴታ አለበት፡፡
3. ደረቅ ቆሻሻ ከሚያነሳለት ድርጅት ጋር ውል በመፈራረም ቆሻሻውን የሚያነሳበትን ቋሚ ፕሮግራም የማሳወቅና በፕሮግራሙ መሰረት የማንሳት ግዴታ አለበት፡፡
4. የተረከበውን ቆሻሻ የአካባቢና የጤና ችግር መንስኤ እንዳይሆን ተገቢውን ጥንቃቄ በመውሰድ የህብረተሰቡን ጤና እና የአካባቢ ደህንነት መጠበቅ አለበት፡፡
5. ደረቅ ቆሻሻን ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውጭ ሰብስቦ ወደ ከተማው ማስወገጃ ቦታ፤ የቆሻሻ ማቃጠያ ወይም የኮምፖስት ማዕከላት ማስገባት የለበትም፡፡
6. ከኤጀንሲው ጋር የተዋዋለውን ውል ለማቋረጥ ሲፈልግ ከማቋረጡ በፊት አንድ ወር ሲቀረው ለውል ሰጪው በጽሁፍ ማሳወቅ ይገባዋል፡፡

7. በውሉ ተመላክቶ በተሰጠው የስራ ቦታ ብቻ አገልግሎቱን የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡
8. የመኪና መበላሸት ቢገጥመው በአፋጣኝ ሌላ መኪና በትውስትም ይሁን በኪራይ በመመደብ አገልግሎቱ እንዳይቋረጥ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
9. አገልግሎት በሚሰጠው ተቋም የተለየውንና ለመልሶ መጠቀም የሚውለውን ደረቅ ቆሻሻ በማንሳት ለሚረከብ አካል መስጠት ወይም እራሱም መጠቀም አለበት፡፡
10. የደረቅ ቆሻሻ ማጓጓዣ ተሽከርካሪዎቹ ከስራ ውጪ (እረፍት) ሲሆኑ የሚያርፉበት (የፓርኪንግ አገልግሎት የሚያገኙበት) ቦታ በኪራይ ወይም በግል (በይዞታ) ማዘጋጀት አለበት፤ የቆሻሻ ማንሻ ተሽከርካሪዎችን በመንገድ ዳር፣ በሰፈር መሀል ወይም ባልተፈቀደ ቦታ ማቆም የለበትም ፡፡
11. አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ መሰብሰብና ማጓጓዝ የለበትም፤
12. ደረቅ ቆሻሻን በአይነት ለይቶ (ለመልሶ መጠቀም፣ ለኃይል ማመንጫ እና ለላንድፊል የሚውል ደረቅ ቆሻሻ) መሰብሰብና ማጓጓዝ አለበት፤
13. በላንድፊል፣ በኃይል ማመንጫ ወይም በመልሶ መጠቀም ኡደት ማዕከላት የሚወጡ ህጎችን (አሰራሮችን) አክብሮ ቆሻሻን ማጓጓዝ አለበት፤
14. ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብና በማጓጓዝ ለሚያሰማራቸው ሰራተኞቹ የስራ ላይ ደህንነት መጠበቂያ አልባሰት ማሟላት ወይም እንዲያሟሉ ማድረግ አለበት ፡፡
15. ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብና በማጓጓዝ የሚያሰማራቸው ሰራተኞች ደንበኞችን (ተቋማትን) በጥሩ ስነ-ምግባርና የስራ ላይ ደህንነት አልባሳቶቻቸውን ንጽሕና ጠበቅው እንዲያገለግሉ ማድረግ አለበት፤

## 11. <u>አገልግሎቱን የሚያገኙ ተቋማት ተግባርና ኃላፊነት</u>

### ማንኛውም ተቋም፡-

1. ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ በዓይነት በመለየት ቆሻሻ ለሚያነሳለት የግል የጽዳት ድርጅት የማስረከብ ግዴታ አለበት፤
2. ያመነጨውን ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን ሳይበክል ኤጀንሲው በሚያወጣው የማጠራቀሚያ ስታንዳርድ መሰረት የማጠራቀም ግዴታ አለበት፡
3. ለግል የጽዳት ድርጅቶች ተጨማሪ ወይም በድርድር ምንም ዓይነት ክፍያ አይከፍልም፤

4. ማንኛውም ተቋም ቆሻሻ ከሚሰበስብለት የግል የጽዳት ድርጅት ጋር ውል ተፈራርሞ ቆሻሻው እንዲነሳለት የማድረግና በየወሩ ለተነሳለት ቆሻሻ ማረጋገጫ የመስጠት ግዴታ አለበት፡

## ክፍል አራት፡

## ግዴታ፣ እርምጃ እና ተጠያቂነት

12. **ግዴታዎች**

ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት፡-

1. ኤጀንሲው በድልድል የተሰጡት ተቋማት የሚያመነጩትን ደረቅ ቆሻሻ አይነትና መጠን መሰረት ሳያደርግ አገልግሎቱን በስታንዳርዱ መሰረት የመስጠት ግዴታ አለበት፤
2. ኤጀንሲው ከሚከፍላቸው ክፍያ ውጪ ከተቋማት ጋር ተደራድሮ ምንም አይነት ተጨማሪ ክፍያ ማስከፈል የለበትም፤
3. ኤጀንሲው ካስቀመጠው የማስወገጃ፣ የማቃጠያ ወይም የኮምፖስት ማዕከል ውጭ ከተቋማት የተሰበሰበን ደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ የተከለከለ ነው፤
4. በላንድፊሉና በኃይል ማመንጫ የተከለከሉ በዕድ ነገሮች (ደንጋይ፣ አፈር፣ ጭቃ፣ የእንጨት ግንድላ ወይም ጉቶ፣ የመንገድና የግንባታ ፍርስራሽ ቆሻሻ፣ ብረታብረት፣ መስታዎትና ብርጭቆ ስብርባሪ) ብቻቸውን ወይም ከሌላ የተቋማት ቆሻሻ ጋር ቀላቅሎ ወደ ላንድፊልና ኃይል ማመንጫ ማጓጓዝ አይችልም፤
5. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ክልል ውጪ ደረቅ ቆሻሻን ወደ አዲስ አበባ ማጓጓዝና ማስወገድ አይችልም ፡፡
6. አደገኛ ደረቅ ቆሻሻ ለመሰብሰብና ለማጓጓዝ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ማግኘት አለበት፤
7. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር አካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ፈቃድ ካልተሰጠው በስተቀር አደገኛ ቆሻሻ ከሚያመነጩ ጤና ተቋማት (ሆስፒታሎች)፣ ቆዳ ፋብሪካዎች፣ መጠጥ ፋብሪካዎች፣ ጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች፣ ወዘተ አደገኛ ደረቅ ቆሻሻን ወደ ላንድፊል ወይም ኃይል ማመንጫ ማምጣት የለበትም፤

13.**እርምጃ**

ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት፡-

1. በዚህ መመርያ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (2፣4፣5፣እና7) ላይ የተቀመጡትን ክልከላዎች ተላልፎ ከተገኘ ኤጀንሲው በቀጥታ ውሉ እንዲቋረጥ ያደረጋል፤ በምትኩም ይህ የግል ጽዳት ድርጅት አገልግሎት ይሰጣቸው የነበሩ ተቋማት በሌላ የግል ጽዳት ድርጅት ወይም ድርጅቶች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ያደረጋል፤
2. በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ (1፣3 እና 6) ላይ የተቀመጡትን ክልከላዎች ተላልፎ ከተገኘ ኤጀንሲው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እንዲሰጠው ያደርጋል፤

14.ተጠያቂነት

ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት

1. የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት ከሚሰጠው ተቋም የአገልግሎት ክፍያ ተቀብሎ ከተገኘ ከኤጀንሲው የወሰደውን የአገልግሎት ክፍያ እንዲመልስ ይደረጋል፤ ኤጀንሲው የሰጠውን የስራ ፈቃድና የብቃት መረጋገጫ እንዲነጠቅ ተደርጎ ለአንድ አመት ከስራ ይታገዳል፤
2. ወደ ደረቅ ቆሻሻ ማስወገጃ ቦታ (ላንድፊል)፣ ደረቅ ቆሻሻ ማቃጣያ ማዕከል እና መልሶ መጠቀምና ኡደት ማዕከል እንዳይጓጓዙ የተከለከሉ አደገኛ ደረቅ ቆሻሻዎችን ሲያጓጉዝ ከተገኘ ኤጀንሲው የሰጠውን የስራ ፈቃድና የብቃት መረጋገጫ እንዲነጠቅ ተደርጎ ለአንድ አመት ከስራ ይታገዳል፤
3. ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ወሰን ውጪ ወደ ከተማ አስተዳደሩ ክልል ደረቅ ቆሻሻ ሲያጓጉዝ ከተገኘ ኤጀንሲው የሰጠውን የስራ ፈቃድና የብቃት መረጋገጫ እንዲነጠቅ ተደርጎ ለሁለት አመት ከስራ ይታገዳል፤
4. በኤጀንሲው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶት በድጋሚ በተመሳሳይ ጥፋት ላይ ከተገኘ ኤጀንሲው የሰጠውን የስራ ፈቃድና የብቃት መረጋገጫ እንዲነጠቅ ተደርጎ ለ6 ወር ከስራ ይታገዳል፤

# ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

15. የሥራ ውል ስለማቋረጥ

1. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት በዚህ መመሪያ አንቀጽ 12 ስር የተዘረዘሩትን የስራ ግዴታዎችን ሳይተገብርና አሰራሮችን ጥሶ ሲገኝ የስራ ውሉ ይቋረጣል፤
2. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት በአገልግሎት አሰጣጡ ግድፈት (ችግር) ታይቶበት አገልግሎት ከሚሰጠው ተቋም እና አገልግሎቱን ከሚሰጥበት ክፍለ ከተማና ወረዳ ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት ቅሬታዎች ከቀረቡበትና በኤጀንሲው የቃል እና የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ እርምጃዎች ከተወሰዱበትና ችግሩን ማስተካከል ካልቻል ከኤጀንሲው ጋር ያለው የአገልግሎት ውል በማንኛውም ጊዜ ይቋረጣል፤
3. ማንኛውም የግል ጽዳት ድርጅት ይሰጥ የነበረውን ደረቅ ቆሻሻ የመሰብሰብና የማጓጓዝ አገልግሎት በተለያዩ ችግሮች መስጠት የማይችልበት ሁኔታ ሲፈጠር አገልግሎት መስጠት እንደሚያቆም ለኤጀንሲው በደብዳቤ ካላሳወቀ በማንኛውም ጊዜ የስራ ውሉ ይሰረዛል፤
4. ኤጀንሲው ከተቋማት ደረቅ ቆሻሻን የመሰብሰብና የማጓጓዙን ስራ በሌላ መንገድ ማከናወን ሲፈልግ ከግል ጽዳት ድርጅቶች ያለውን የኮንትራት ስራ ውል ማቋረጥ ይችላል፤ ነገር ግን የነበረውን ውል ማቋረጥ ሲፈልግ ለግል ጽዳት ድርጅቱ ከሁለት ወር ቀድሞ ማሳወቅ አለበት፡፡

16. <u>ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች</u>

ከዚህ መመርያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመርያና ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመርያ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

17. <u>መመሪውያውን ስለማሻሻል</u>

ይህ መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በኤጀንሲው ሊሻሻል ይችላል፡፡

18. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ በፍትህ ሚኒስቴር ተመዝግቦ በድረገጽ ላይ ከተጫነበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሚያዝያ/ 2016ዓ.ም

ዶ/ር እሸቱ ለማ

ዋና ዳይሬክተር

የአዲስ አበባ ከተማ የጽዳት አስተዳደር ኤጀንሲ

## ቅጥያ አንድ (annex one) ፡

### የግል ጽዳት ድርጅቶች አገልግሎት መስጫ ድርጊት መርሃ ግብር

### ቅጽ 001

| ተ.ቁ | የተቋሙ ስም | ተቋሙ የሚገኝበት አድራሻ | | | | ቆሻሻ የሚነሳበት ቀናት | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ክ/ከተማ | ወረዳ | ቀጠና | ስልክ ቁጥር | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሀሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |
| | | | | | | | | | | | | |

**ቅጥያ ሁለት** (annex two)፥

የግል ጽዳት ድርጅቶች አገልግሎት ከሚሰጧቸው ተቋማት አገልግሎቱን በአግባቡ ስለመስጠታቸው ከተቋማቱ በየወሩ የሚያቀርቡት ማረጋገጫ ቅጽ 002

1. ክፍለ ከተማ-----------ወረዳ----------የግል ጽዳት ድርጅቱ ስም--------
   የተቋሙ ስም፡ ------------------
2. ቆሻሻ የተነሳበት ቀን-------------------- ሰዓት--------------- የተሽከርካሪ ሰሌዳ ቁጥር----------
3. የግል ጽዳት ድርጅቱ ተወካይ/ሹፌር ስም------------------ ስልክ ቁጥር----------
   - ከላይ በተገለጸው ቀንና ሰዓት የተቋማችን ቆሻሻ መነሳቱን እናረጋግጣለን፡፡

   የተቋሙ ባለቤት/ተወካይ ስም--------------------ፊርማ-----------ቀን---------------

3. **ቅጥያ ሶስት** (annex three)፥- የግል ጽዳት ድርጅት ስለሚሰጡት አገልግሎት ጥራት በክትትልና ድጋፍ ስራዎች በወረዳ ጽዳት አስተዳደር ጽ/ቤት በየወሩ የሚሞላ ቅጽ 003

የግል ጽዳት ድርጅቱ ስም ----------------------------------------

| ተ.ቁ. | በወረዳው በግል ጽዳት ድርጅቱ አገልግሎት የሚሰጣቸው ተቋማ ብዛት | በስታንዳርዱ መሰረት አገልግሎት ያገኑ ብዛት | በአገልግሎት አሰጣጡ ቅሬታ ያላቸው (ያቀረቡ) ብዛት | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሆቴሎች | | | |
| 2 | የገባያ ማዕከላት | | | |
| 3 | ፋብሪካዎችና ኢንዱስትሪዎች | | | |
| 4 | ጤና ተቋማት | | | |
| 5 | ለሎች ድርጅቶች (የሸቀጣሸቀጥ ሱቆች፣ ቁርስ ቤቶች፣ ት/ቤቶች፣ ዳቦ ቤቶች፣ ሱፐር ማርኬቶች፣ ካፌ ቤቶች፣ የተለያዩ ቢሮዎች፣ ወዘተ) | | | |